**የአቶ ታዬ ጉልላት የቀብር ሥነ ሥርዓት እና ፍትሃት /Wake/**

**ቀን**/ Date Oct 11, 2014

**ሰዓት** / Time 9:00 – 12:00

**አድራሻ**/ Address/ St. James Armenian Apostolic Church
465 Mount Auburn St.
Watertown, MA 02472

**ቀብር ሥነርዓት** / Burial Ceremony/

**ሰዓት** / Time 12:00 – 1:30

**አድራሻ** / Address/ Cambridge Cemetery
76 Coolidge Avenue
Cambridge, MA 02138

# አቶ ታዬ ጉልላት
# /ጳውሎስ/



# የአቶ ታዬ ጉልላት አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ ታዬ ጉልላት ከአባቱ ከደጃዝማች ጉልላት ታዬና ከእናቱ ከወ/ሮንጋቷ ኃይሌ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በተስፋ ኮከብ፥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቀጥሎም የዩኒቨርስቲ ትምህረቱን በዩኒቨርስቲ ኦፍ ካሊፎርኒያ፥ ዴቪስ አጠናቋል፡፡



ከ1966 ዓ.ም. አብዮት በኋላ ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገውን ትግል የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ /ኢህአፓ/ ወጣት ክንፍ አባል በመሆን የተቀላቀለ ሲሆን በመጀመሪያ በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢው በነበረውትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚያም የኢህአፓ ሠራዊት አባል በመሆን በትግራይ፥በቤጌምድርና በሰሜን ክፍለ ሃገሮች ውስጥ ሠራዊቱ በመደበው ቦታ ሁሉ በጽናትና በጀግንነት የታገለ ወንድማችን ነበር፡፡

በወቅቱ ለህክምና ትምህርት ወደ ቻይና ተልኮ በአኩፓንቸርና በጠቅላላ የህክምና ሙያ ተጨማሪ ትምህርት ተምሮ ወደ ሜዳ ተመልሷል፡፡ ከዚያም ከሌሎች የድርጅቱ አባላት ጋር በስደት ወደ አሜሪካ በመምጣት ቀደም ሲል ጀምሮት የነበረውን ትግል ቀጥሎ ሕይወቱ እስከ አለፈበት ቀን ድረስ በተለያየ ደረጃ ትግሉን ይጠቅማል ባለበት ሁሉ በንቃት ሲሳተፍ ቆይቷል፡፡

ወንድማችን ታዬ /ጳውሎስ/ ጀግንነትን፥ ፍቅርን፥ ትህትናን፥ጽናትን አጣምሮ የያዘ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ነበር፡፡

በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በአኩፓንቸርና በሌላም የሕክምና አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በእነዚህ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደሚያውቁት የነጻ አኩፓንቸር ዕርዳታና የሕክምና አገልግሎት እየሰጠ ከተለያዩ የነርቭ በሽታዎች እንዲድኑ አድርጓል፡፡

የእኛ ታዬ የጓደኞቹ ደግሞ ጳውሎስ ሳይተርፈው የሚሰጥ፥ ሳይበላ የሚያጎርስ፥ ሕይወቱን በሙሉ ለሌሎች በጎ በመሥራት የኖረ ነበር ስለዚህ ምንም እንኳን ለእኛ በሥጋ ቢወለደንም ጳውሎስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ወንድም በመሆኑ ኃዘኑ የሁላችንም መሆኑ ይታወቃል፡፡ ጳውሎስ ልጆችና የልጅ ልጆች አሉት፡፡

የሰው መለያው በሕይወት እያለ ያከናወነው ተግባሩ ነው፡፡ የጳውሎስን የወገንና የሃገር ፍቅር፥ ቆራጥነትና ጽናት ለምናውቅ ሁሉ ወንድማችን በአካልም ሆነ በመንፈስ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል፡፡



ዛሬ ጳውሎስ ከመካከላችን በሞት በመለየቱ ኃዘናችን የመረረ ቢሆንም ከጓደኞቹና ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የምንጋራው መሆኑ እንድንጽናና ያደርገናል፡፡

ከተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶችና ከካናዳ በአካል በመገኘት የኃዘናችን ተካፋይ ከመሆናችሁም በላይ ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ፥በገንዘብ፥በጉልበትና በሃሳብ ለረዳችሁን ሁሉ እንዲሁ በአካል በመገኘት ያልተለያችሁን፥ በተለያየ የዓለም ክፍሎች ሆናችሁ በስልክ፥ በደብዳቤ፥ እንዲሁም በኢሜል የኃዘናችን ተካፋይ በመሆን እንድንጽናና ያበረታታችሁን ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አምላክ ሁላችንንም ብርታቱን እንዲሰጠን እንለምናለን!!!

ቤተሰቦቹ

ወ/ሮ ምህረት ታዬ ጉልላት<br>
ወ/ት ያበሻወርቅ ግርማ<br>
አቶ ሽመልስ ጉልላት